*መልእክት ሁለት*

## የሞትና የሲኦል መክፈቻ ያለው ክርስቶስ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- ራእ. 1፥17-18፤ 10፥7፤ 12፥11፤ 15፥1፣ 8፤
ሐዋ. 2፥24፤ ፊልጵ. 3፥10-11

**I. "ፊተኛውና [ኋለኛው] ሕያዉም እኔ ነኝ"—ራእ 1፥17-18፡-**

ሀ. ክርስቶስ *ፊተኛው*ና *ኋለኛው* መሆኑ የጀመረውን ነገር እንደሚጨርስ ያመለክታል።

ለ. ጌታ ኢየሱስ *ፊተኛው* ብቻ ሳይሆን *መጀመሪያው*፣ *ኋለኛው* ብቻ ሳይሆን *መጨረሻው*ም ነው—21፥6፤ 22፥13፡-

1. *ፊተኛው* የሚለው ከእርሱ በፊት ማንም እንደሌለ፣ *ኋለኛው* የሚለው ከእርሱ በኋላ ማንም እንደሌለ ያመለክታል።
2. *መጀመሪያው* የሚለው እርሱ የነገሮች ሁሉ መመንጨት መሆኑን፣ *መጨረሻው* የሚለው የነገሮች ሁሉ መጠናቀቅ መሆኑን ያመለክታል።
3. እዚህ ጋር ያለው ምልከታ ከጌታ ኢየሱስ በፊት ወይም በኋላ ምንም አለመኖሩ ብቻ ሳይሆን ያለ እርሱ መመንጨት ወይም መጠናቀቅ አለመኖሩንም ነው።

ሐ. ክርስቶስ ፊተኛውና ኋለኛው ብቻ ሳይሆን መጀመሪያውና መጨረሻውም ነው፤ የጀመረውን የቤተ ክርስቲያን ሕይወት እርሱ እንደሚፈጽመው ይህ ያረጋግጥልናል—ተዛ. 2 ጢሞ 4፥5፡-

1. ጌታ ኢየሱስ *ሥራውን* ሳያጠናቅቅ አይተወውም—ራእ. 10፥7፤ 15፥1፣ 8።
2. አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ጌታ ኢየሱስ መጀመሪያውና መጨረሻው መሆኑን ማመን አለባቸው።
3. በምለሳው የጀመረውን ነገር ይፈጽመዋል።

መ. የአብያተ ክርስቲያናት ራስ የሆነውና አብያተ ክርስቲያናት የእርሱ የሆኑት በአብያተ ክርስቲያናት መካከል የሚመላለሰው ክርስቶስ ሕያዉ ነው፤ ስለዚህ፣ እንደ አካሉ መገለጥ አብያተ ክርስቲያናት ሕያው፣ ትኩስና ጠንካራ መሆን አለባቸው—2፥1።

**II. "ሞቼም ነበርሁ እነሆም፥ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ነኝ"—1፥18፡-**

ሀ. ጌታ ሞቶ እንደገና ሕያው ሆኗል—2፥8።

ለ. ክርስቶስ ወደ ሞት ገባ፣ ነገር ግን እርሱ ትንሣኤ ስለሆነ (ዮሐ. 11፥25) ሞት ይይዘው ዘንድ አልቻለም (ሐዋ. 2፥24)።

ሐ. ትንሣኤ የጌታ ዕድሜ መርዘም ነው፤ እርሱ በትንሣኤው ከዘላለም እስከ ዘላለም ይኖራል፡-

1. ዛሬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕያዉ፣ በትንሣኤ ያለው ነው።
2. ክርስቶስ ሕይወቱን ያድል ዘንድ፣ ሕያዉ መሆን አለበት።

መ. ክርስቶስ ሕያዉ የመሆኑ አስፈላጊነት እርሱ ለዘላለም መኖሩና በእኛ ውስጥ መኖሩ ነው፡-

1. የትኛውንም ዓይነት ሞት ትተን ሕያዋ ቤተ ክርስቲያን ለመሆን እንድንነሣ ይፈልጋል።
2. ይበልጥ ሕያው በሆንን መጠን፣ ይበልጥ ሕያው የሆነው ኢየሱስ ምስክሮች ነን—12፥11።

**III. "በእርሱም ደግሞ ሄዶ በወኅኒ ለነበሩ [መናፍስት] ሰበከላቸው"—1 ጴጥ. 3፥19፡-**

ሀ. እዚህ ጋር *መናፍስት* የሚለው በሲኦል የታሰሩ የሞቱ ሰዎችን አካል የሌላቸውን መናፍስትን ሳይሆን በኖኅ ዘመን ባለመታዘዝ የወደቁትንና በድቅድቅ ጨለማ የታሰሩትን፣ የታላቁን ቀን ፍርድ እየተጠባበቁ ያሉትን መላእክት (መላእክት መናፍስት ናቸው—ዕብ. 1፥14) ያመለክታል—2 ጴጥ 2፥4-5፤ ይሁዳ 6።

ለ. ክርስቶስ በሥጋ ከሞተ በኋላ መለኮታዊውን እቅድ ለማበላሸት በነበረው የሰይጣን ሴራ ላይ በክርስቶስ ተሠግዎና በክርስቶስ ሞት የተከናወነውን የእግዚአብሔርን ድል ለመስበክ መለኮትነቱ በሆነው በሕያው መንፈሱ እነዚህ ዓመጸኛ መላእክት ወዳሉበት ወደ ጥልቁ ሄደ።

ሐ. *ወኅኒ* (1 ጴጥ. 3፡19) የሚያመለክተው እንጦርጦስን፣ የወደቁ መላእክት ታስረው የሚገኙበትን የጥልቁንና የጨለማውን ጉድጓዶች ነው።

**IV. "ከሰማይም ወደ ምድር ወድቆ የነበረ ኮከብ አየሁ፥ የጥልቁም ጉድጓድ መክፈቻ ተሰጠው"—ራእ. 9፥1-2፣ 11፥7፣ 17፥8፣ 20፥1፣ 3፡-**

ሀ. በራእይ 9፥1 ያለው ኮከብ ከሰማይ ወደ ምድር የሚጣለውን ሰይጣንን ያመለክታል፡-

1. መላእክቱ በከዋክብት ተመስለዋል—ኢዮ. 38፥7፤ ራእ. 12፥4።
2. እንደ የመላእክት አለቃ ሰይጣን የአጥቢያ ኮከብ ነበር—ኢሳ. 14፥12።

ለ. “ወደ ጥልቁ ማን ይወርዳል?...ይህ ክርስቶስን ከሙታን ለማውጣት ነው”—ሮሜ 10፥7፦
1. “ጥልቅ” ተብሎ የተተረጎመው ቃል በግሪኩ "አቢሶስ" ነው።
2. ይህ ቃል የአጋንንትን የመኖሪያ ስፍራ በማመልከት በሉቃስ 8፥31 ጥቅም ላይ ውሏል—ቁ. 27፣ 33፣ 35፣ 38።
3. ንጉሣቸው አፖልዮን የሆነው “አንበጣዎች” የሚመጡበትን ስፍራ ለማመልከት በራእይ 9፥1-12 እና 11ም ይገኛል።
4. በራእይ 11፥7 እና 17፥8 አውሬው፣ የክርስቶስ ተቃዋሚው የሚወጣበትን ስፍራ ያመለክታል።
5. በራእይ 20፥1 እና 3 በሺው ዓመት ዘመን ሰይጣን ተጥሎ የሚታሰርበትን ስፍራ ያመለክታል።
6. በሮሜ 10፥7 *ጥልቅ* የሚለው ክርስቶስ ከሞቱ በኋላና ከትንሣኤው በፊት የነበርንውን ስፍራ ያመለክታል፤ ይህም ስፍራ፣ በሐዋርያት *ሥራ* 2፥24 እና 27 *መሠረት*፣ ሲኦል ነው፣ ምክንያቱም ሐዋ 2፥24 እና 27 ክርስቶስ ከሞተና በትንሣኤው ከዚያ ስፍራ ከተነሣ በኋላ ወደ ሲኦል እንደሄደ ይገልጣሉና።
7. በመጽሐፍ ቅዱሳዊ አጠቃቀም *መሠረት*፣ *ጥልቅ* የሚለው ቃል ሁልጊዜም የሚያመለክተው ክርስቶስ ከሞተ በኋላ ወደ አሸነፈው ወደ ምድር ታችኛው ክፍል የወረደበትን (ኤፌ 4፥9) እና በትንሣኤው ከዚያ የዐረገበትን የሞት ክልልና የሰይጣንን የጨለማ ኃይል ነው።

## V. በራእይ 1፥18 ጌታ ኢየሱስ “የሞትና የሲኦል መክፈቻ አለኝ” ይላል፦

ሀ. ከሰው ውድቀትና ኃጢአት የተነሣ፣ ሞት ገብቷል፣ አሁንም ኃጢአተኛ ሰዎችን ሁሉ ለመሰብሰብና ሙታን ወደ ሚቀመጡበት ሲኦል ለማምጣት በምድር ላይ እየሠራ ነው።

ለ. በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ግን ከእንግዲህ ለሞትና ለሲኦል አንገዛም—ፊልጵ. 3፥10-11።

ሐ. ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሞትን ሽሮታል፣ በትንሣኤውም ሲኦልን ድል ነሥቷል፦
1. ክርስቶስን ይዞ ለማስቀረት ሞት የተቻለውን ሁሉ ቢጥርም፣ ያንን ለማድረግ አቅም አልባ ነበር—ሐዋ. 2፥24።
2. ክርስቶስ የማይጠፋውን ሕይወት የያዘ (ዕብ. 7፥16) እግዚአብሔርም ትንሣኤም ነው (ዮሐ 1፥1፤ 11፥25)።
3. እርሱ ለዘላለም የሚኖረው ስለሆነ፣ ሞት ይይዘው ዘንድ አይችልም።
4. ክርስቶስ ራሱን ለሞት አሳልፎ ሰጠ፣ ነገር ግን ሞት እርሱን የሚይዝበት ምንም ዓይነት መንገድ አልነበረውም፤ በምትኩ፣ ሞት በእርሱ ተሸነፈ፣ እርሱም ከሞት ተነሣ።
5. ስለዚህ፣ በክርስቶስ ዘንድ ሞት መውጊያ የለውም፣ ሲኦልም ኃይል የለውም።

መ. ክርስቶስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሞትና የሲኦል መክፈቻ ያለው ስለሆነ፣ ሞትና ሲኦል በእኛ ላይ ምንም ኃይል ሊኖራቸው አይገባም።

ሠ. በቤተ ክርስቲያን ሕይወት የሞትና የሲኦል መክፈቻ በጌታ እጅ ውስጥ ናቸው።

ረ. ለእኛ ሞትን ማስወገድ የማይቻል ነገር ነው፦
1. ሞትን የምናስወግድበት ችሎታ ፈጽሞ የለንም።
2. ሞት በገባ ጊዜ ሁሉ፣ ብዙዎች በእርሱ ይሸነፋሉ።

ሰ. ጌታ ኢየሱስ በመካከላችን እንዲንቀሳቀስና እንዲሠራ ስፍራ እድልና ነጻ መንገድ ከሰጠነው፣ ሞትም ሲኦልም በቁጥጥሩ ሥር ይሆናሉ—ማቴ. 16፥18፤ ራእ. 20፥14፦
1. ጌታ ኢየሱስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስፍራ ሲያገኝ፣ ሞት ወዲያውኑ አሸናፊ ይሆናል፣ ሲኦልም ሙታንን ለመያዝ ኃያል ይሆናል።
2. ክርስቶስ የሞትና የሲኦል መክፈቻ፣ ሥልጣን እንዳለው ማየታችን ወሳኝ ነው—ዮሐ. 5፥27፤ 17፥2፤ ራእ. 12፥10።
3. ሞት ለእርሱ ተገዝቷል፣ ሲኦልም በቁጥጥሩ ሥር ነው።

ሸ. ክርስቶስ የሞትና የሲኦል መክፈቻ ስላለው ጌታን ማወደስ አለብን—1፥18፤ ዕብ. 13፥15፣ 1 ጴጥ. 1፥7፤ ራእ. 19፥5-6።

© 2025 Living Stream Ministry